


**ቁጥር 29/2002 ታህሳስ 07 ቀን 2002 ዓ.ም.**

# *የህዳር ወር የአየርና የግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ሁኔታና ከታህሳስ ወር የአየር ሁኔታ አዝማሚያ አንፃር በአርሶአደሩ፣ በአርብቶ አደሩና በከፊል አርብቶ አደሩ ሊወሰዱ የሚገባቸው እርምጃዎች*

## ሀ. የህዳር ወር 2002 ዓ.ም የአየርና የግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ሁኔታ

### 1. የዓየር ሁኔታ

በህዳር ወር በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች የነበረውን የዓየር ሁኔታ አስመልክቶ ከተለያዩ ምንጮች በተገኙ መረጃዎች መሠረት በወሩ በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ እንደነበረና ዝናቡ በሶስተኛው አስር ቀናት ውስጥ የስርጭት አድማሱን ከማስፋቱም በላይ በአንዳንድ ቦታዎችም የተመዘገበው ዝናብ ከፍተኛ መጠን ያለው እንደነበረ ተጠቁሟል፡፡

በክልሎች የነበረውን የአየር ሁኔታ በተመለከተ:-

- በኦሮሚያ ብ/ክ/ መንግስት በወሩ የመጀመሪያ አስር ቀናት ውስጥ ደረቅና ፀሐያማ ሆኖ የሰነበተ ሲሆን በወሩ ሁለተኛው አስር ቀናት ውስጥ ከፊል ኢሉአባቦራ (6 ወረዳዎች)፣ ቄለም ወለጋ (1 ወረዳ)፣ ምስ/ወለጋ (6 ወረዳዎች)፣ ቦረና (2 ወረዳዎች) ዞኖች ከካፊያ እስከ ዝቅተኛ መጠን ያለው ዝናብ መዝነቡ እንዲሁም በወሩ ሶስተኛው አስር ቀናት ውስጥ ዝናቡ በቦታ ሽፋኑና በመጠኑ ጨምሮ በኢሉአባቦራ፣ ጂማ፣ ምስ/ወለጋ፣ ምዕ/ወለጋ፣ ምዕ/ሸዋ፣ ጉጂና ቦረና ዞኖች ሁሉንም ወረዳዎች ያዳረሰ ከአነስተኛ እስከ ከፍተኛ መጠን ያለው ዝናብ የጣለ መሆኑ እንዲሁም ከፊል ምዕ/ሸዋ (ሶዶ ዳጪ ወረዳ)፣ ምዕ/አርሲ (8 ወረዳዎች)፣ አርሲ (21 ወረዳዎች)፣ ባሌ (11 ወረዳዎች)፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ (8 ወረዳዎች)፣ ምዕ/ሐረርጌ (14 ወረዳዎች)፣ ምስ/ሐረርጌ (12 ወረዳዎች)፣ ቦረና (አባያ ወረዳ) እና ጉጂ (6 ወረዳዎች) ዞኖች ከአነስተኛ እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ የዘነበ መሆኑ፣

- በደቡብ ብ/ብ/ህ/ብ/ክ/ መንግስት በወሩ የመጀመሪያው አስር ቀናት ውስጥ በከፋና ጌዴኦ ዞኖች ሁሉንም ወረዳዎች የሸፈነ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ የዘነበ ሲሆን ከፊል ወላይታ (ዳሞት ወይዴና ሶዶ ዙሪያ ወረዳዎች)፣ ሲዳማ (አሮሬሳ ወረዳ)፣ ቤንች ማጂ (8 ወረዳዎች)፣ ደ/ኦሞ (5 ወረዳዎች)፣ ጋሞጎፋ (8 ወረዳዎች)፣ ሸካ (2 ወረዳዎች) ዞኖችና ከፊል ባስኬቶና ከፊል ኮንሶ ልዩ ወረዳዎች ከዝቅተኛ እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ መዝነቡ፣ በወሩ ሁለተኛው አስር ቀናት ጌዴኦ ዞን በሁሉም ወረዳዎች ከፊል ከፋ (5ወረዳዎች)፣ ጋሞጎፋ (6ወረዳዎች)፣ ቤንች ማጂ (8 ወረዳዎች)፣ ደ/ኦሞ (4 ወረዳዎች)፣ ሲዳማ (8 ወረዳዎች) ዞኖችና ከፊል ደራሼ ልዩ ወረዳ (6 ቀበሌዎች) ከካፊያ እስከ ዝቅተኛ መጠን ያለው ዝናብ፣ በወሩ ሶስተኛው አስር ቀናት በሀዲያ፣ ከምባታ ጠምባሮ፣ ወላይታ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ማጂ፣ ዳውሮ፣ ሲዳማ፣ ጌዴኦና ደ/ኦሞ ዞኖች ሁሉንም ወረዳዎች የሸፈነ፣ የምና ኮንሶ ልዩ ወረዳዎች ደግሞ ሁሉንም ቀበሌዎች ያዳረሰ



በግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር
ቅድሚያ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ዳይሬክቶሬት
አዲስ አበባ
ስልክ ቁ0115509666 ፋክስ 0115525111 ኢሜይል agromet.moa@telecom.net.et ፖ.ሳ.ቁ. 62347 አ.አ

ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ መጠን ያለው ዝናብ የዘነበ መሆኑ፣ ከፊል ጋሞጎፋ (6 ወረዳዎች)፣ ጉራጌ (3 ወረዳዎች) ዞኖችና ከፊል ሀላባ (56 ቀበሌዎች)፣ አማሮ (7 ቀበሌዎች)፣ ባስኬቶ (15 ቀበሌዎች)፣ ኮንታ (32 ቀበሌዎች)፣ ደራሼና (4 ቀበሌዎች) ቡርጂ (2 ቀበሌዎች) ልዩ ወረዳዎች ከዝቅተኛ እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ የዘነበ ሲሆን ስልጤ ዞን በወሩ ውስጥ ዝናብ ያልዘነበ መሆኑ፣

- በትግራይ ብ/ክ/ መንግስት የወሩ የመጀመሪያውና ሁለተኛው አስር ቀናት ደረቅና ፀሀያማ ሆኖ የሰነበተ ሲሆን በወሩ ሶስተኛው አስር ቀናት ውስጥ በምስራቃዊ ዞን ጉሎመኸዳ ወረዳ ሁሉንም ቀበሌዎች የሸፈነ በከፊል ጋንታ አፈሹም ወረዳ (11 ቀበሌዎች)፣ በደ/ምስራቅ ዞን እንደርታ ወረዳ (1 ቀበሌ)፣ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ መዝነቡና በደቡባዊ ዞን አላማጣና ራያ አዘቦ ወረዳዎች አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበ መሆኑ፣

- በአማራ ብ/ክ/ መንግስት የመጀመሪያው አስር ቀናት ደረቅና ፀሐያማ የአየር ሁኔታ ሰፍኖ የሰነበተ መሆኑ፣ በወሩ ሁለተኛው አስር ቀናት ውስጥ በምስ/ጎጃምና ኦሮሚያ ዞኖች ሁሉንም ወረዳዎች ያዳረሰ እንዲሁም በከፊል ሰ/ጎንደር (6 ወረዳዎች)፣ ደ/ወሎ (ሳይንት ወረዳ) እና አዊ (ከጃዊ ወረዳ በስተቀር) ከካፊያ እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ የዘነበ ሲሆን በወሩ ሶስተኛው አስር ቀናት ውስጥ ዋግህምራ ዞን ዳህና ወረዳና ሰ/ወሎ ዞን ጉባላፍቶ ወረዳ ላይ ካፊያ የነበረና አብዛኛው የክልሉ አካባቢ ደመናማ እንደነበር፣

- በሱማሌ ብ/ክ/ መንግስት በመስከረም ወር ሶስተኛው አስር ቀናት ውስጥ አብዛኛዎቹን የዴር ዝናብ ተጠቃሚ የሆኑትን ዞኖች (ደገሀቡር፣ ፊቅ፣ ቆራሄ፣ ሊበንና ጎዴ) እንዲሁም የዴር ዝናብ ተጠቃሚ ያልሆኑትን ጂጂጋና ሽንሌ ዞኖችን ጨምሮ ሰፋ ያሉ አካባቢዎችን በመሸፈን ቀደም ብሎ የጀመረው የዴር ዝናብ እስከ ጥቅምት ሁለተኛው አስር ቀናት መጨረሻ ድረስ መዝነቡ፣ ሆኖም ዝናቡ ቀጣይነት ሳይኖረው በጥቅምት ሶስተኛው አስር ቀናትና በህዳር ወር እስከ አጋማሹ ድረስ ደረቅና ፀሀያማ የአየር ሁኔታ አመዝኖ መሰንበቱ፣ ይሁንና ሰፍኖ የነበረው ደረቅና ፀሀያማ የአየር ሁኔታ ከህዳር 18 ቀን ጀምሮ በነበሩት ሶስት ተከታታይ ቀናት ውስጥ በቀጠለው ዝናብ በመተካቱ በዚሁ ጊዜ መጠኑ ከቦታ ቦታ የተለያየ ዝናብ መዝነቡ፣

- በአፋር ብ/ክ/ መንግስት የወሩ የመጀመሪያውና ሁለተኛው አስር ቀናት ደረቅና ፀሀያማ ሆኖ የሰነበተ ሲሆን በወሩ ሶስተኛው አስር ቀናት ውስጥ ግን በዞን 5 እና 1 ከአነስተኛ እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ የዘነበ መሆኑ እንዲሁም

- በጋምቤላ ብ/ክ/ መንግስት ስርጭቱ ያልተስተካከለ አነስተኛ ዝናብ የተመዘገበ መሆኑ፣ ከየክልሉ ከተሰበሰቡ የክትትል መረጃዎች ታውቋል፡፡

## 2. የግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ሁኔታ
### 2.1. ሰብል ልማት

በህዳር ወር መኸር አብቃይ በሆኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች አርሶ አደሩ የራሱንና የቤተሰቡን ጉልበት በማስተባበር እንዲሁም ወቅታዊ ባልሆነ ዝናብ ምክንያት በደረሱ ሰብሎች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ሕብረተሰቡን በማስተባበር በዘመቻ መልክ (ተማሪዎች፣ መምህራን፣ ወዘተ.) የሰነበቱ ሲሆን በእርጥብ ወይና ደጋና ደጋማ አካባቢዎች ደግሞ ሰብል በመድረስና በመሰብሰብ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ የክትትል መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በወሩ የዘነበው ዝናብ አንዳንድ ቦታዎች የአጨዳ ስራን ለአጭር ጊዜ ከማስተጓጎሉ (ለምሳሌ በአርሲ ዞን አንዳንድ ቦታዎች) በስተቀር ቀጣይነት ስላልነበረው በሰብል ላይ የጎላ ጉዳት ስለማድረሱ ከየትኛውም የክትትል መረጃ ከተሰበሰበባቸው የሀገሪቱ አካባቢዎች የቀረበ ሪፖርት የለም፡፡



በግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር
ቅድሚያ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ዳይሬክቶሬት
አዲስ አበባ
ስልክ ቁ0115509666 ፋክስ 0115525111 ኢሜይል agromet.moa@telecom.net.et ፓ.ሳ.ቁ. 62347 አ.አ

በሌላ በኩል በወሩ የዘነበው ዝናብ በእርጥብ ወ/ደጋና በደጋማ አካባቢዎች ለተዘሩ ሰብሎች እንዲሁም በአንዳንድ ቦታዎች የመኸሩ ዝናብ ዘግይቶ ከመግባቱ ጋር ተያይዞ ዘግይተው ለተዘሩ ሰብሎች ቀጣይ እድገት ምቹ ሁኔታ ከመፍጠሩም ሌላ በዝናብና በመስኖ በመታገዝ በቀጣይ ለሚለሙ ሰብሎች የመሬት ዝግጅትና በደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልል በከፋ፣ ቤንች ማጂ፣ ሸካና ዳውሮ ዞኖች በቆሎ ለመዝራትና በሌሎች ዞኖች ደግሞ ለስራስር ሰብሎች ተከላ እገዛ ማድረጉ ታውቋል፡፡

በየክልሉ የነበረውን የሰብል ልማት ሁኔታ በተመለከተ:-

- በአማራ ብ/ክ/ መንግስት በመኸሩ ወቅት በዘር ከተሸፈነው 3,967,081 ሄ/ር መሬት ውስጥ እስካሁን ድረስ 2,735,525 ሄ/ር ወይም 69 በመቶ የሚሆነው መሬት የታጨደ ሲሆን ቀሪዎቹ በደጋማና ወ/ደጋማ አካባቢዎች የሚገኙ ሰብሎች አጨዳም የቀጠለ መሆኑ፣ በክልሉ ደ/ወሎና ሰ/ሸዋ ዞኖች በቀጣዩ የበልግ ወቅት ለማልማት ከታቀደው እንደቅደም ተከተላቸው 119,610 እና 79,879 ሄ/ር መሬት ውስጥ በወሩ 48,990 ሄ/ር እና 7,373 ሄ/ር የታረሰ መሆኑ፣

- በኦሮሚያ ብ/ክ/ መንግስት በደ/ምዕ/ሸዋ፣ ጂማ፣ ኢሉአባቦራ፣ ምዕ/አርሲ፣ ሰ/ሸዋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ምዕ/ሸዋ፣ ምስ/ወለጋ፣ ምዕ/ወለጋ፣ ምስ/ሸዋና አርሲ ዞኖች ሰብል በአብዛኛው በአጨዳና በአንዳንድ አካባቢዎችም በመድረስ ላይ እንደሚገኝ፣ በባሌ ዞን (ሰብል አብቃይ አካባቢዎች) በአበባና በእሸት ደረጃ ላይ እንደሚገኝ፣ ይህ በዚህ እንዳለ በባሌ ዞን አርብቶ አደር ወረዳዎችከዝናብ እጥረት ጋር በተያየዘ በአጋጠመው የእርጥበት ችግር ምክንያት በሰብል ላይ ጉዳት የደረሰ መሆኑ፣

- በትግራይ ብ/ክ/ መንግስት የሰብል አጨዳ በአብዛኛው የተጠናቀቀ መሆኑና የቀሩትም ማሳዎች በታህሳስ ወር የመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት ውስጥ ታጭደው የሚጠቃለሉ መሆናቸው፣ በወሩ በክልሉ አንዳንደ አካባቢዎች በነበረው ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ በመጠቀም ለቀጣይ የምርት ወቅት የመሬት ዝግጅት መደረጉ፣

- በደቡብ ብ/ክ/ መንግስት በአብዛኛዎቹ ዞኖችና ልዩ ወረዳዎች ቆላና ወ/ደጋ አካባቢዎች የመኸር ሰብል በመሰብሰብ እንዲሁም ቡና ተለቅሞ በመጠናቀቅ ላይ ሲሆን በሲዳማና ጌዴኦ ዞኖች ደጋና ወ/ደጋማ አካባቢዎች የተዘሩ ሰብሎች ፍሬ በመሙላትና በእሸት ደረጃ ላይ መገኘታቸው፣ በወሩ የጣለው ዝናብ በደረሱ ሰብሎች ላይ የጎላ ጉዳት አለማድረሱ፣ በሌላ በኩል በከፋ፣ ቤንች ማጂ፣ ሸካና ዳውሮ ዞኖችና በኮንታና የም ልዩ ወረዳዎች የበልግ በቆሎ ዘር ስራ በስፋት የተጀመረ መሆኑ እንዲሁም በወላይታ፣ ደ/ኦሞና ዳውሮ ዞኖች ስኳር ድንችና ሌሎችም የስራ ስር ሰብሎች በመተከል ላይ መሆናቸው፣ በወሩ የተገኘው ዝናብ ቀድመው ለተዘሩትና በቡቃያ ደረጃ ለሚገኙት ሰብሎች እድገት አስተዋፅኦ ማድረጉ፣ ይህ በዚህ እንዳለ በኮንሶ፣ አማሮ፣ ደራሼና ቡርጂ ልዩ ወረዳዎች ቆላማ አካባቢዎች የተዘሩ የበቆሎ፣ ማሽላ፣ ጤፍ፣ ስንዴና አደንጓሬ ሰብሎች በቂ ዝናብ ባለማግኘታቸው ከ75% እስከ 100% ለጉዳት መዳረጋቸው፣

- በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብ/ክ/ መንግስት አብዛኛዎቹ ቦታዎች በቆሎና ሰሊጥ የተሰበሰበ ሲሆን ማሽላ ፍሬ በመሙላትና በመብሰል ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑ፣

- በሀረሪ ብ/ክ/ መንግስት የመኸር ሰብል በቆላማ አካባቢ የተሰበሰበ ሲሆን በወ/ደጋማ አካባቢ በብስለት ላይ የሚገኝ መሆኑ፣

- በሶማሌ ብ/ክ/ መንግስት በጂጂጋ አካባቢ የሚገኙ ከፊል አርብቶአደሮችና አርሶአደሮች ከዝናቡ እጥረት ጋር በተያያዘ ቶሎ ደራሽ ስንዴና ገብስ ሰብሎችን የዘሩ ሲሆን ከዚህም ደህና ምርት ይገኛል ተብሎ የሚጠበቅ መሆኑ፣



በግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር
ቅድሚያ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ዳይሬክቶሬት
አዲስ አበባ
ስልክ ቁ0115509666 ፋክስ 0115525111 ኢሜይል agromet.moa@telecom.net.et ፖ.ሳ.ቁ. 62347 ኢ.አ

- በአፋር ብ/ክ/ መንግስት የመስኖ ልማት የመሬት ዝግጅት በመደረግ ላይ መሆኑ፣

- በድሬዳዋ አስተዳድር ማሽላ ታጭዶ በመወቃት ላይ መሆኑ፣

- በጋምቤላ ብ/ክ/ መንግስት በውሃ ሸሽ ማሳዎች ላይ የተዘሩ የበቆሎና የማሽላ ሰብሎች በቡቃያና በእድገት ደረጃ ላይ የሚገኙ መሆናቸው፣ ከየክልሎቹ የተገኙ የክትትል መረጃዎች ጠቁመዋል::

## 2.2. የተዛማች ፀረ-ሰብል ተባይ ክስተት

- **የበረሐ አንበጣ**

  በወሩ የበረሀ አንበጣ በአማራ ብ/ክ/ መንግስት በሰ/ወሎ ዞን መቄት ወረዳ ውስጥ ተከስቶ ጉዳት ከማድረሱ በፊት በ470 ሄ/ር መሬት ላይ የኬሚካል ርጭት በማድረግ መከላከል የተቻለ መሆኑን የክትትል መረጃዎች ጠቁመዋል::

- **ግሪሳ ወፍ**

  በህዳር ወር በአማራ ብ/ክ/ መንግስት ሰሜን ሸዋ ዞን አንጾኪያ ወረዳ ግማሽ ሚሊዮን እንዲሁም በኦሮሚያ ዞን ዳዋጨፋ ወረዳ 900 ሺ ያህል የሚገመት የግሪሳ ወፍ ወረርሽኝ በሳር ላይ ተከስቶ በድምሩ 250 ሊትር ፀረ ወፍ ኬሚካል በመርጨት ከ95 እስከ 99 በመቶ የተሳካ መከላከል የተደረገ መሆኑ፣ በዚህ ረገድ ባለንበት አመት ከመስከረም ወር መጨረሻ ሳምንት ጀምሮ እስካሁን ድረስ በኦሮሚያ፣ በደቡብ ብ/ብ/ህ/ እና በአማራ ክልሎች በድምሩ 10.4 ሚሊየን የሚገመት የወፍ መንጋ ተከስቶ 700 ሊትር ፀረ ወፍ ኬሚካል በመርጨት ከ98 በመቶ በላይ የተሳካ መከላከል መደረጉን ከክትትል መረጃዎች ታውቋል::

## 2.3. የእንስሳት ሁኔታ

የክትትል መረጃ በተሰበሰበባቸው አብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች የግጦሽና የውሀ አቅርቦት በቂ የነበረ መሆኑ ተጠቁሟል:: በተለይም በመኸር አብቃይ አካበቢዎች የሰብል ተረፈ ምርት የሚገኝበትና በወሩ በበርካታ የሀገሪቱ አካባቢዎች የነበረው ወቅቱን ያልጠበቀው ዝናብ የእንስሳት ግጦሽ/መኖ እና ውሃ አቅርቦትን በማሻሻል ረገድ የጎላ አስተዋፅ እንደሚኖረው ይታመናል:: ይሁን እንጂ ከበልጉ ወቅት የዝናብ ሁኔታ መዛባትና ከመኸሩ ወቅት ዘግይቶ መግባትና አልፎ አልፎም መቆራረጥና የመጠን ማነስ ጋር ተያይዞ የእንስሳት ግጦሽ እና/ወይም የውሃ እጥረት በአንዳንድ ቦታዎች ላይ አለመቃለሉን መረጃዎቹ አመልክተዋል:: ከእዚህም አካባቢዎች መካከል:-

- በአፋር ብ/ክ/ መንግስት ኤሊዳር፣ ኮሪ፣ ቢዱና አረፐቲ ወረዳዎች፣

- በደቡብ ብ/ብ/ሕ ብ/ክ/ መንግስት በወላይታ ዞን ዱጉና ፋንጎ፣ ሁምቦና ዳሞት ወይዴ ወረዳዎች፣ በሲዳማ ዞን ቦሪቻና ሎካአባያ ወረዳዎች፣ በጋሞጎፋ ዞን ምዕ/አባያ፣ ዛላና፣ ኡባ ደብረ ፀሀይ ወረዳዎች ቆላማ ቦታዎችና በኮንሶ፣ አማሮ፣ ደራሼና ቡርጂ ልዩ ወረዳዎች፣



በግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር
ቅድሚያ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ዳይሬክቶሬት
አዲስ አበባ
ስልክ ቁ0115509666 ፋክስ 0115525111 ኢሜይል agromet.moa@telecom.net.et ፓ.ሳ.ቁ. 62347 አ.አ

- በአማራ ብ/ክ/ መንግስት በሰሜን ጎንደር ዞን ጠለምት፣ ጃንአሞራና፣ ምስራቅ በለሳ ወረዳዎች፣ በሰሜን ሸዋ ዞን ቀወትና ምንጃር ሸንኮራ ወረዳዎች፣ በሰሜን ወሎ ዞን ቆቦ፣ ላስታና ግዳን ወረዳዎች፣ በዋግ ህምራ ዞን ዝቋላ፣ አበርገሌና ሳህላ ወረዳዎች፣

- በኦሮሚያ ብ/ክ/ መንግስት በባሌ ዞን ጊኒርና ጎሎልቻ ወረዳዎች፣ በምስ/ሐረርጌ ዞን ሚደጋ፣ መዩ ፣ ቁምቢና ጎላኦዳ ወረዳዎች፣ በቦረና ዞን ሞያሌ ፣ ሚዮና ተልተሌ ወረዳዎች፣

- በትግራይ ብ/ክ/ መንግስት ደቡባዊ ዞን አላማጣ፣ ራያ አዘቦና ህንጣሎ ዋጅራት ወረዳዎች፣ በምስራቃዊ ዞን ክልተ አውላእሎ ወረዳ፣ በሰሰሜን ምዕራብ ዞን አስገደ ፅምብላ ወረዳ፣

- በጋምቤላ ብ/ክ/ መንግስት ጆር ወረዳ፣ የሚገኙበት መሆኑ ከተሰበሰቡት መረጃዎች ታውቋል::

- ከዚህም በተጨማሪ በሶማሌ. ብ/ክ/ መንግስት አብዛኛዎቹ የሽንሌ ዞን ወረዳዎች፣ በጂጂጋ ዞን ሀርሺን ወረዳ፣ በጎዴ ዞን ዳናን ወረዳ፣ በዋርዴር ዞን ጋላዲ እና ዋርዴር ወረዳዎች፣ በፊቅ ዞን ሳላሃድ፣ ማዮሙሉኮና ላጋሂዳ፣ ዱሁን እና ከፊል ሰገግ ወረዳዎች ከዝናብ እጥረት ጋር በተያያዘ ተመሳሳይ ችግር እንዳለ ከክልሉ የተገኘ መረጃ ጠቁሟል::

## 2.4. የተዛማች የእንስሳት በሽታዎች ፍንዳታ ክስተት ሁኔታ

- በወሩ ተዛማች የእንስሳት በሽታ ፍንዳታ ስለመከሰቱ ከየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል የቀረበ ሪፖርት የለም::

## 2.5. የደን እሳት ቃጠሎ ክስተት

- በወሩ የደን ቃጠሎ ስለመከሰቱ ከየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል የቀረበ ሪፖርት የለም::

## 2.6. የሌሎች አደጋዎች ክስተት ሁኔታ

- በወሩ በኦሮሚያ ብ/ክ/ መንግስት የውርጭ አደጋ በሰሜን ሸዋ ዞን ቅምብቢት ወረዳ በ9150 ሄ/ር የገብስ ሰብል ላይ 9%፣ በ8842 ሄ/ር የስንዴ ሰብል ላይ 12%፣ በ7570 ሄ/ር የባቄላ ሰብል ላይ 15% ፣ በሆሮጉድሩ ወለጋ ዞን በአባቦጉድሩ ወረዳ በ9 ሄ/ር የበቆሎ ሰብል ላይ 69%፣ በምስ/ሐረርጌ ዞን በሀሮማያ ወረዳ በ460 ሄ/ር መሬት ላይ በነበሩ የተለያዩ ሰብሎች ላይ 25-50 % ጉዳት ማድረሱ፣
- በአማራ ብ/ክ/ መንግስት ሰ/ወሎና ሰ/ሸዋ ዞኖችና በደቡብ ብ/ብ/ ህዝቦች ክልል በጉራጌ ዞን ጉመር ወረዳ ውርጭ ተከስቶ በተለያዩ ሰብሎች ላይ አነስተኛ ጉዳት ማድረሱ ከየክልሎቹ የተገኘ መረጃ ይጠቁማል::



በግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር
ቅድሚያ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ዳይሬክቶሬት
አዲስ አበባ
ስልክ ቁ0115509666 ፋክስ 0115525111 ኢሜይል agromet.moa@telecom.net.et ፖ.ሳ.ቁ. 62347 አ.አ

## ለ. የታህሳስ ወር የአየር ሁኔታ አዝማሚያና በአርሶ አደሩ፣ በአርብቶ አደሩና በከፊል አርብቶ አደሩ ሊወሰዱ የሚገባቸው ተከታታይ እርምጃዎች

### 1. የታህሳስ ወር የዓየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በታህሳስ ወር በአብዛኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች ደረቅና ፀሐያማ የአየር ሁኔታ የሚዘወተርበት እንዲሁም በደጋማ አካባቢዎች ላይ የሌሊትና የማለዳ ቅዝቃዜ የሚጠናከርበት ጊዜ ነው። ይሁን እንጂ እ.አ.አ የታህሳስ ወር 2009 የአየር ሁኔታ አዝማሚያን አስመልክቶ ብሔራዊ የሜቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ በሰጠው መረጃ መሰረት የህንድና የአትላንቲክ ውቅያኖሶች እንዲሁም የአረብና የሜዲትራንያን ባህሮች ከመደበኛው በላይ በመሞቅ ላይ የሚገኙ በመሆናቸውና ክስተቱም ለዝናብ መኖር ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር በመሆኑ ባለንበት ታህሳስ ወር የስምጥ ሸለቆና አጎራባች አካባቢዎች፣ የደቡብ ምእራብ፣ የደቡብ፣ የመካከለኛው፣ የምሥራቅና የሰሜን ምሥራቅ አካባቢዎችን ጨምሮ በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ የመኖር እድሉ ከፍተኛ እንደሚሆን ተጠቁሟል፡፡

በአጠቃላይ እንደ ኤጀንሲው መረጃ ባለንበት ታህሳስ ወር ምሥራቅ ትግራይ፣ መካከለኛውና ምሥራቅ አማራ፣ ምእራብና ደቡብ ኦሮሚያ፣ ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ህዝቦች ክልል ምሥራቅና መካከለኛ ኢትዮጵያ እንዲሁም ጋምቤላ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ የማግኘት እድል የሚኖራቸው ሲሆን፣ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ደቡባዊ አጋማሽና የሶማሌ ደቡባዊ ክፍል ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ዝናብ ያገኛሉ። ቀሪዎቹ አካባቢዎች በአብዛኛው ደረቅ ሆነው ይቆያሉ።

### 2. በአርሶ አደሩ፣ በአርብቶ አደሩና በከፊል አርብቶ አደሩ ሊወሰዱ የሚገባቸው ተከታታይ እርምጃዎች

#### 2.1. ሰብል ልማትን በተመለከተ:-

በታህሳስ ወር የሚከናወኑት የሰብል ልማት ተግባራት ከቦታ ቦታ የተለያዩና ቀደም ባሉት ወራቶች ከተከናወኑት ተግባራት ጋር ተከታታይነት ያላቸው ናቸው፡፡ ስለሆነም በያዝነው ታህሳስ ወር ከሚኖረው የዓየር ሁኔታ አኳያ አርሶ አደሩ፣ ከፊል አርብቶ አደሩና የእነርሱ አጋዥ የሆኑ የግብርና ልማት ባለሙያዎች ለሚከተሉት ተግባራት ተገቢውን ትኩረት መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡

- በወሩ ከሚከናወኑት የሰብል ልማት ተግባራት መካከል የደረሱ ሰብሎችን መሰብሰብና መውቃት አጠናክሮ መቀጠል ወሳኝ ተግባር ነው፡፡ በዚህ ረገድ የስምጥ ሸለቆና አጎራባች አካባቢዎች፣ የደቡብ ምእራብ፣ የደቡብ፣ የመካከለኛው፣ የምሥራቅና የሰሜን ምሥራቅ አካባቢዎችን ጨምሮ በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል የኤጀንሲው መረጃ የጠቆመ በመሆኑ አርሶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደሩ የራሱንና የቤተሰቡን ጉልበት በማስተባበር እንዲሁም የሚመለከታቸው አካላት የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን በማስተባበር በዘመቻ መልክ በማንኛውም የአየሩ ሁኔታ አመች ሆኖ በተገኘበት ጊዜ ሁሉ የደረሱ ሰብሎችን ፈጥኖ በመሰብሰብ እስኪወቃ ድረስ በዝናብ ጉዳት ሊደርስበት በማይችል መልኩ በአግባቡ መከመር ይጠበቅባቸዋል፡፡



በግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር
ቅድሚያ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ዳይሬክቶሬት
አዲስ አበባ
ስልክ ቁ0115509666 ፋክስ 0115525111 ኢሜይል agromet.moa@telecom.net.et ፖ.ሳ.ቁ. 62347 አ.አ

- ሰብል ከተሰበሰበ በኋላ ለረዥም ጊዜ ከምሮ ማቆየት ለዝናብና ለተባይ ጥቃት ስለሚዳርግ በተቻለ መጠን በማንኛውም ጊዜ በሚኖረው ፀሐያማ የዓየር ሁኔታ በመታገዝ ንፅህናው በተጠበቀ አውድማ ላይ በወቅቱ መውቃት አስፈላጊ ነው::

- የታጨደ ሰብል ከማሳ ወደሚከመርበት ቦታ፣ ከተከመረበት ቦታ ለውቂያ ወደ አውድማ እንዲሁም ከተወቃ በኋላ ወደ ማከማቻ ቦታ በሚጓጓዝበት ጊዜ ብክነት እንዳይኖር ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግለት ስለሚገባ አርሶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደሩ ይህንኑ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል::

- እህል ጎተራ ወይም መጋዘን ውስጥ ከመግባቱ በፊት ጥራቱ የተጠበቀና በሚገባ የደረቀ መሆኑ ተረጋግጦ ከተባይ ነጻ በሆነና በእርጥበት ወይም በሙቀት ኃይል ሊባክን በማይችልበት ጎተራ ወይም መጋዘን ውስጥ መከማቸት ስለሚኖርበት በዚህ ረገድ አርሶ አደሩ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ይገባዋል:: በተጨማሪም የተከማቸ እህል በጎተራ ተባዮች ክስተት ሳቢያ ጉዳት እንዳይደርስበትና እንዳይባክን አስፈላጊውን ክትትልና የመከላከል እርምጃ በወቅቱ መውሰድ ያስፈልጋል::

- ሰብል እንደተሰበሰበ ማሳን ወዲያውኑ ማረስ ለቀጣይ የተሟላ የማሳ ዝግጅትና ሰብልን ከነፍሳት ተባይ፣ ከበሽታና ከአረም ጥቃት መከላከል ከሚያስችሉ ዘዴዎች አንዱ በመሆኑ አርሶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደሩ በወሩ ይህንን ተግባር ለማከናወን አመች ሁኔታን በሚፈጥር የዓየር ሁኔታ በመታገዝ በወቅቱ ማከናወን ይጠበቅበታል::

- በልግ አብቃይ በሆኑ አካባቢዎች በወሩ ትኩረት ከሚሰጣቸው ተግባራት መካከል ለበልግ ሰብሎች የማሳ ዝግጅትን ማከናወን በመሆኑ ለዚህ ተግባርም የተለየ ትኩረት መስጠት ይገባል:: በተጨማሪም በነዚሁ አካባቢዎች የበልጉ ዝናብ እንደጀመረ ወዲያውኑ ዘር መዝራት እንዲቻል ከወዲሁ የምርት ግብዓቶች አቅርቦትን መጀመሩ አስፈላጊ ስለሆነ በዚህ ረገድ የሚመለከታቸው ክፍሎች ተገቢውን እርምጃ በወቅቱ መውሰድ ይገባቸዋል::

- ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ዝናብ እንደሚያገኙ በተጠቆሙት የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ደቡባዊ አጋማሽና የሶማሌ ደቡባዊ ክፍል በማንኛውም ጊዜ የሚገኘውን እርጥበት በማሰባሰብ ለግብርና ስራዎች ጥቅም ላይ ለማዋል ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፣

- በሌላ በኩል በወሩ በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች እንደሚከሰት የተተነበየው ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ደቡብና ደቡብ ምስራቅን ጨምሮ በአንዳንድ የሀገሪቱ ቆላማ አካባቢዎች ቀደም ሲል የነበረውን የዝናብ እጥረት በመቅረፉ ረገድ አስተዋፅኦ ይኖረዋል:: በመሆኑም የተለያዩ የውሃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎችን በመጠቀም በማንኛውም ጊዜ የሚገኘውን ዝናብ ማሰባሰብና ለግብርና ልማት ስራዎች ለማዋል መንቀሳቀስ ለዘላቂ ውጤት አስፈላጊ ነው፡፡

- በበጋ ወቅት ውሃ ገብ በሆኑ አካባቢዎች አነስተኛ የመስኖ ልማት እንቅስቃሴ በስፋት የሚካሄድበት ጊዜ በመሆኑ በያዝነው ወር የመስኖ ቦዮችን ማፅዳት፣ የማሳ ዝግጅትን ማከናወን፣ የዘር አቅርቦት ዝግጅት ማድረግና የችግኝ ማፍላትና ማዛመት እንዲሁም በቀጥታ የሚዘሩትን መዝራት በአርሶ አደሩ ልዩ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ናቸው::



በግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር
ቅድሚያ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ዳይሬክቶሬት
አዲስ አበባ
ስልክ ቁ0115509666 ፋክስ 0115525111 ኢሜይል agromet.moa@telecom.net.et ፓ.ሳ.ቁ. 62347 አ.አ

## 2.2. የተዛማች ፀረ-ሰብል ተባይ ክስተትን በተመለከተ:-

- የበረሐ አንበጣ

ባሳለፍነው ህዳር ወር በተገኘው መረጃ መሰረት የበረሀ አንበጣ በአማራ ክልል ሰሜን ወሎ ዞን ተከስቶ ቁጥጥር የተደረገበት ሲሆን በያዝነው ታህሳስ ወርም ተባዩ ሊከሰትባቸው ይችላሉ ተብለው በሚጠረጠሩ ክልሎችና አካባቢዎች የክትትሉንና የአሰሳውን ሥራ በአንበጣ አሳሽ እስካውቶች፣ በግብርናና ገጠር ልማት ባለሙያዎችና አርሶ አደሮች /ከፊል አርብቶ አደሮች ተሳትፎ አጠናክሮ በመቀጠል ተባዩ እንደታየ ወዲያውኑ በአቅራቢያ ለሚገኝ የግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት ሪፖርት ማድረግ ያስፈልጋል::

- ግሪሣ ወፍ

በታህሳስ ወር በመደበኛ ሁኔታ በየትኛውም የሀገሪቱ አካባቢ የግሪሳ ወፍ ወረርሽኝ ክስተት አይጠበቅም::

## 2.2. የእንስሳት ሁኔታን በተመለከተ:-

ከክትትል መረጃዎች መረዳት እንደተቻለው ባሳለፍነው ህዳር ወር ከውስን ቦታዎች በስተቀር በአብዛኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች በቂ የእንስሳት መኖና ውሃ አቅርቦት ነበር:: ወሩ መኸር አብቃይ በሆኑ የሀገሪቱ ክፍሎች የሰብል ተረፈ ምርት የሚገኝበት ከመሆኑም ሌላ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ የነበረበት ጊዜ በመሆኑ የእንስሳት መኖ/ግጦሽና የውሃ አቅርቦት ሁኔታን በተወሰነ ደረጃ ማሻሻሉ ተጠቁሟል:: ይሁን እንጂ በበጋ ወቅት በብዙ የሀገሪቱ አካባቢዎች በዝናብ እጥረት ምክንያት የእንስሳት የመጠጥ ውሃና የመኖ ችግሮች ሊያጋጥም እንደሚችል ይታወቃል:: ስለዚህ በወቅቱ የተገኘውን የመኸር ሰብል ተረፈ ምርት ለእንስሳት መኖ በቁጠባ መጠቀም ችግሩን በማቃለል ረገድ የጎላ አስተዋፅኦ ይኖረዋል::

በተጨማሪም በአየር ሁኔታ አዝማሚያ ጥቆማው መሰረት በህዳር ወር የነበረው ወቅቱን ያልጠበቀው ዝናብ ባለንበት ታህሳስ ወርም በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ቀጥሎ የመዝነብ እድሉ ከፍተኛ በመሆኑና ዝናቡ በከፊል አርብቶ አደርና አርብቶ አደር አካባቢዎች ለእንስሳት ውሃና ግጦሽ አቅርቦት ጠቀሜታ ስለሚኖረው አስፈላጊውን ዝግጅት በማድረግ የተገኘውን እርጥበት በአግባቡ መጠቀም ያስፈልጋል:: ከዚህም ሌላ ከመደበኛ የተቀራረበ ወይም ያነሰ ዝናብ እንደሚያገኙ በተጠቆሙት የሀገሪቱ አካባቢዎችም የተለያዩ ውሃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎችን በመጠቀም በማንኛውም ጊዜ የተገኘውን ውሃ በማሰባሰብ ለእንስሳት ጥቅም ማዋል አስፈላጊ ነው::

## 2.3. የደን እሳት ቃጠሎ ክስተትን በተመለከተ:-

ባለንበት ታህሳስ ወር በሀገሪቱ በርካታ አካባቢዎች ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ የመከሰት እድሉ ከፍተኛ መሆኑ በሜቲዎሮሎጂ ትንበያ የተጠቆመ በመሆኑ ሁኔታው ለደን እሳት ክስተት አመች እንደማይሆን ይታመናል:: ይህም ሆኖ ደረቅና ፀሀያማ የአየር ሁኔታ በሚያመዝንባቸው አካባቢዎች በተለያዩ ምክንያቶች በህብረተሰቡ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች የደን ቃጠሎን እንዳያስከትሉ የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ተገቢው ጥንቃቄ እንዲደረግ ለሕብረተሰቡ ትምህርትና ወቅታዊ መልእክት ሊያስተላልፉ ይገባል::



በግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር
ቅድሚያ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ዳይሬክቶሬት
አዲስ አበባ
ስልክ ቁ0115509666 ፋክስ 0115525111 ኢሜይል agromet.moa@telecom.net.et ፖ.ሳ.ቁ. 62347 አ.አ

## 3. ማጠቃለያ

በአጠቃላይ በያዝነው ታህሳስ ወር ከሚኖረው የዓየር ሁኔታ አኳያ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ዙሪያ መወሰድ የሚገባቸውን ተከታታይ እርምጃዎች ከአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በተገናዘበ መልኩ በወቅቱ ተግባራዊ ማድረግ ይገባል። ከዚህ ጋር በተያያዘም በየደረጃው የሚገኙ የግብርና ልማት ባለሙያዎችና የሥራ ሃላፊዎች አስፈላጊውን ሙያዊ እገዛና የተጠናከረ የምክር አገልግሎት መስጠት ይጠበቅባቸዋል።



በግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር
ቅድሚያ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ዳይሬክቶሬት
አዲስ አበባ
ስልክ ቁ0115509666 ፋክስ 0115525111 ኢሜይል agromet.moa@telecom.net.et ፓ.ሳ.ቁ. 62347 አ.አ